# የMINNESOTA የሚከፈልበት ፈቃድ

ከጃንዋሪ 1፣ 2026 **ጀምሮ ተፈፃሚ የሚሆን**

## ለራስዎ ወይም ለቤተሰብዎ እንክብካቤ ለመስጠት የእረፍት ጊዜ ሲፈልጉ የMinnesota የሚከፈልበት ፈቃድ ክፍያዎች እና የስራ ጥበቃዎችን ያቀርባል።

### ተመጣጣኝ ዕቅዶች

አሰሪዎ የሚከፈልበት ፈቃድ የሚሰጠው Minnesota ስቴት በኩል ይልቅ በተፈቀደ ተመጣጣኝ ዕቅድ በኩል ነው። ይህ ዕቅድ Minnesota የሚከፈልበት ፈቃድ ከሚሰጡት ጋር ተመጣጣኝ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የእረፍት ጊዜያት፣ ክፍያዎችና የስራ ጥበቃዎችን ይሰጣል።

የመድን ሰጪው ስም፦ ______________________________

ተመጣጣኝ ዕቅድ የሚሸፍነው፦ ☐ የቤተሰብ ፈቃድ ☐ የሕክምና ፈቃድ ☐ ሁለቱም

ድረ-ገጽ፦____________________ ስልክ፦ ____________________

### የሚከፈልበትን ፈቃድ ለምን አላማ ልጠቀምበት እችላለሁ?

የሕክምና ፈቃድ፦

- **ከእርግዝና፣** ከወሊድ እና ከማገገም ጋር የተገናኙትን ጨምሮ ለራስዎ ከባድ የጤና እክል እንክብካቤ ለማድረግ

የቤተሰብ ፈቃድ፦

- **የትስስር ፈቃድ –** በውልደት፣ በጉዲፈቻ ወይም የማደጎ ምደባ በኩል ለመጣ አዲስ ልጅ እንክብካቤ ለማድረግ እና ትስስር ለመፍጠር
- **የእንክብካቤ ፈቃድ –** ከባድ የጤና እክል ላለበት የቤተሰብ አባል እንክብካቤ ለማድረግ
- **የውትድርና የቤተሰብ ፈቃድ –** ለግዳጅ ለተጠራ የቤተሰብ አባል ድጋፍ ለማድረግ
- **የደህንነት ፈቃድ –** በራስዎ ወይም በቤተሰብ አባል ላይ የደረሰ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ማሰቃየት ጋር የተገናኙ ችግሮች ላይ ምላሽ ለመስጠት

በአጠቃላይ፣ ሁኔታዎች ቢያንስ ለሰባት ቀናት የሚዘልቁ እና በጤና እንክብካቤ አቅራቢው ወይም በሌላ ባለሙያው የተረጋገጡ መሆን አለባቸው።

### በሚከፈልበት ፈቃድ ሽፋን አገኛለሁ?

በMinnesota ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ሰራተኞች በሚከፈልበት ፈቃድ ሽፋን ያገኛሉ። የአሰሪዎ መጠን ወይም እርስዎ የሚሰሩበት ሰዓታት ወይም ቀናት ምንም ይሁን ምን ሽፋን ያገኛሉ። ገለልተኛ ሥራ ተቋራጮች እና በግል የሚሰሩ ግለሰቦች በራስ-ሰር ሽፋን አያገኙም፤ ነገር ግን መርጠው ሊገቡ ይችላሉ። ባለፈው ዓመት በMinnesota ውስጥ አነስተኛ የስራ መጠን ክፍያ ከተከፈለዎት፣ ለክፍያዎች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ (2026 የሚከፈልበት ፈቃድ መነሻ፣ $3,900 ያህል)።

### ለምን ያህል ጊዜ ፈቃድ መውሰድ እችላለሁ?

ተመጣጣኝ ዕቅድ በስቴቱ ከሚሰጠው ጋር እኩል ወይም የበለጠ የፈቃድ ጊዜ መስጠት አለበት። በስቴቱ ዕቅድ መሰረት፣ በጥቅማ ጥቅም ዓመቱ እስከ 12 ሳምንታት የሚቆይ የቤተሰብ ወይም የሕክምና ፈቃድ ለመውሰድ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚያው የጥቅማ ጥቅም ዓመቱ ላይ የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ በአጠቃላይ እስከ 20 ሳምንታት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

### ምን ያህል ይከፈለኛል?

ተመጣጣኝ ዕቅድ በስቴቱ ከሚሰጠው ጋር እኩል ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክፍያዎችን መክፈል አለበት። በስቴቱ ዕቅድ መሰሠረት፣ እስከ 90% የሚደርስ ደመወዝዎ የሚከፈልዎት በገቢ ደረጃዎ መሰረት ሲሆን ከፍተኛው ሳምንታዊ መጠን ደግሞ በስቴቱ አማካይ ሳምንታዊ ደመወዝ በተቀመጠው መሰረት ነው። ይህ መጠን በየዓመቱ የሚለዋወጥ ሲሆን በ2026 ለሚከፈልበት ፈቃድ መነሻ $1,423 ነው።

### ለዚህ ሽፋን የሚከፍለው ማነው?

የMinnesota የሚከፈልበት ፈቃድ በሰራተኞች እና አሰሪዎች በሚከፈሉ ፕሪሚየሞች የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል። አሰሪዎ የተመጣጣኝ ዕቅድ ፕሪሚየምን ክፍያ ለመደገፍ ሲል ከደመወዝዎ 0.44% በላይ መጠን ሊያስከፍልዎ አይችልም።

### የእኔ የቅጥር ጥበቃዎች ምንድን ናቸው?

- የስራ ጥበቃዎች፦ በአጠቃላይ፣ ከፈቃድ ሲመለሱ ወደ ስራዎ ወይም ተመጣጣኝ የስራ መደብ መመለስ ይገባዎታል። የስራ ጥበቃዎች ከተቀጠሩበት ቀን አንስቶ የ90 ቀናት ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ።
- የጤና መድን መቀጠል፦ በአጠቃላይ፣ እርስዎ በእረፍት ላይ እያሉ አሰሪዎች የራሳቸውን የጤና እንክብካቤ መድን ፕሪሚየሞችን ድርሻ የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸውን መቀጠል አለባቸው።
- ምንም አይነት በቀል ወይም ጣልቃገብነት አለመኖር፦ እርስዎ ለሚከፈልበት ፈቃድ ካመለከቱ ወይም ከተጠቀሙ አሰሪዎች ጣልቃ መግባት ወይም የበቀል ተግባር መፈፀም የለባቸውም። አሰሪዎች የእርስዎን የሚከፈልበት እረፍት ክፍያዎች መውሰድ አይችሉም።

ከሚከፈልበት እረፍት ጋር ለተገናኙ ጥያቄዎች፣ እባክዎ የMinnesota የሚፈልበት እረፍትን በ 651-556-7777 ያነጋግሩ ወይም የእኛን የድር ጣቢያ ይጎብኙ። በMinnesota የሥራ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ (Department of Labor and Industry) ውስጥ ያሉትን የሰራተኛ ስታንዳርድስ ክፍል (Labor Standards Division) ያነጋግሩ

**ተጨማሪ ይወቁ፦** paidleave.mn.gov

ይህ መረጃ ለአካል ጉዳተኛ ወይም የቋንቋ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች በ 651-556-7777 ወይም 844-556-0444 (ከክፍያ ነፃ) በመደወል በአማራጭ ቅርጸቶች ሊሰጥ ይችላል።

MINNESOTA PAID LEAVE

12/2025

Minnesota Paid Leave | 180 E 5th St Suite 1200 | Saint Paul, MN 55101